# ሚሲዮናዊ የህይወት ታሪክ

## ዮሃንስ ጉተንበርግ -- የትውልድ ዘመን፡ 1398 - 1468

መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር እና በሰው ልጆች መካከል ያለ ታላቅ የፍቅር ታሪክ ነው፤ ይህንም ሰው ሁሉ ሊሰማው ይገባል። ቅዱሳት መጻሕፍት በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት የተጻፉ ለትምህርት፣ ለተግሣጽ፣ ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ የሚጠቅሙ ናቸው። ታላቁና ጥንታዊው መጽሐፍ ወደ እኛ መጥቷል ምክንያቱም ብዙ ታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎች የሆኑ ወንዶች እና ሴቶች ጥንታዊ ጽሑፎችን በመመርመር፣ በመቅዳት እና በዘመናዊ ቋንቋዎች ለመተርጎም ራሳቸውን መስዋዕት ሰላደረጉ ነው። ከብዙዎቹ መካከል አንዱ ደግሞ ዮሃንስ ጉተንበርግ ነበር።

ዮሃንስ ጉተንበርግ በ1450 የዓለማችንን የመጀመሪያውን ማተሚያ የፈጠረ ጀርመናዊ አንጥረኛ፣ አታሚ እና አሳታሚ ነበር። የተወለደው በጀርመን ማይንዝ በተባለ ከተማ ነው፤ ለወላጆቹ እና ሀብታም ጓደኞቻቸው የእጅ ጽሑፎችን ማንበብ ያስደስተው ነበር። የመጽሐፍ ባለቤት የሚሆኑት ሀብታሞች ብቻ በመሆናቸው ግን ያዝን ነበር። ከእነዚህም ስሜቶቹ በመነሳት ቀላል እና ፈጣን የህትመት መንገድ ለማዘጋጀት ወሰነ። በስትራስበርግ የፈራረሰ ሕንፃ ተከራይቶ የማተሚያ ማሽን ለመሥራት ልዩ ልዩ ሀሳቦችን መሞከር ጀመር። ገንዘቡ ሲያልቅ ከሌላ ወርቅ አንጥረኛ ጆአሃን ፉስት ገንዘብ ተበድሮ መስራት ቀጠለ በመጨረሻም የአስደናቂው ፈጠራው የመጀመሪያ ውጤት እንዲሆን መጽሐፍ ቅዱስን መረጠ።




በ1455 እያንዳንዳቸው ሦስት መቶ ገጾች ያሉት አንድ የሚያምር የላቲን መጽሐፍ ቅዱስ በሁለት ጥራዞች ማተም ቻለ። ሆኖም ጉተንበርግ ከዚህ ድንቅ ስራ ምንም አይነት ትርፍ አላመጣም ምክንያቱም ማሽኑ በጆአሃን ፉስት እጅ ገብቶ ስለነበር ነው።

የጉተንበርግ የማተሚያ ማሽን ፈጠራ የመጽሐፍ ቅዱስ ህትመት እና የወንጌል ስርጭትን አቀጣጥሏል። መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ሳይሆን ማሽኑ እንደ ማርቲን ሉተር እና ጆን ካልቪን የመሳሰሉት የፕሮቴስታንት የተሐድሶ ሰዎች በጽሑፎቻቸው ማገልገል እንዲጀምሩ ረድቷቸዋል። መጽሐፍ ቅዱስ ለብዙሃን መታተሙ እያንዳንዱ አማኝ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲያነብ እድል የከፈተ ሲሆን፣ ይህም እያንዳንዱ ሰው ለራሱ መዳን ተጠያቂ እንደሆነ ያሳያል። የጉተንበርግ ጥረት ክርስትና በቤተክርስቲያን ደጃፍ ላይ ብቻ ሳያበቃ የእያንዳንዱን አማኝ ቤት የስልጠና ሜዳ እንዲሆን አድርጓል።

ወዳጅ ሆይ፣ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለው የፍቅር ታሪክ በሁሉም ሰው ዘንድ እንዲሰማ እያደረግክ ነው?

“ጌታ ሆይ፣ በእጄ እና በቤቴ ስላለኝ መጽሐፍ ቅዱስ አመሰግንሃለሁ። ለመንግሥትህ እድገት አስተዋጽዖ ይሆን ዘንድ በዙዎች ጋር መጽሐፍ ቅዱስ እንዲደርስ ድርሻዬን እንድወጣ እርዳኝ። አሜን!”

እጣሪ: ዶክተር ሄፕሲባህ ሴልቫም